# ጠመናል አትበሉ

ከተሻለ መንግሥቱ (ለንደን)

ቆብ ጭናችሁ ገዳም፡ ከተማ የአላችሁ፤
በደም አትግደፉ፡ ተፈታ ብላችሁ።

የሐዋሪያትን ቃል፡ እናንት ከያዛችሁ፤
በጾም ሁዳዴ፡ ዓለምን አሥራችሁ፤
በሥጋ አትግደፉ፡ ጠመናል ብላችሁ።

ሱባዔ ሣትይዙ፡ በፍትሐዘወልድ፤
እያጋደላችሁ፡ ዘመድ ከባዕድ።

እሳት አንድዳችሁ፡ ለመጭው ትውልድ፡
ጠመናል አትበሉ፡ ሳታበቁ ቀልድ።

ሥራችሁ ግብራችሁ፡ ሰውን የሚያነድ፤
ሱሰኛ ሆናችሁ፡ የቁማር ላይ ቀልድ፤
ብዙ ታምር አዩን፡ በናንተ ትውልድ።

በቃ ተመለሱ፡ ወደ ተዋሕዶ፤
ሕይወት ወደሰጠን፡ እራሱን አዋርዶ።

እስቲ ተመልከቱ፡ የቱ ነው ክብራችሁ፡
በሱ መከበር ነው፡ ወርደት በሆዳችሁ።

ብታስቡትማ፡ ቆቡ የራሳችሁ፤
ማስታወሻ ነበር፡ ለማላ ቃላችሁ፤
ሞቱን ልትሞቱ፡ ዕውነት መሥክራችሁ።

ትንቢቱ እንዲፈጸም፡ ዘመን ከአመጣችሁ፤
የናንተን ቃልኪዳን፡ ለሕጻን ሰጣችሁ፤
በውግዘት መታኮስ፡ ሆነ ጸሎታችሁ።

ለሞተው ነፍስ ይማር፡ እግዚኦ ብላችሁ፤
ለታመመው ምሕረት፡ ኪዳናት ደግማችሁ፤
እስሩን ሳትፈቱ፡ ስምአኒ ብላችሁ፤
ጠመናል ብትሉ፡ ማንም አያምናችሁ።

Posted on www.debteraw.com on 03 April 2007 by courtesy of the poet

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

Posted on www.debteraw.com on 03 April 2007 by courtesy of the poet

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com